ፓኖራማ ቁጥር 91

**የትዝብት አድማስ**

ሰኔ 16 ቀን 2002 ዓም

## <u>ከእንግዲህ ምን ይኮን ?</u>

በሰው ልጆች ነፃነት፥ ፍትኀ-ርትዕ ፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፥ የህግ የበላይነትና በመልካም አስተዳደር የሚያምነው የመላው ዓለም ሕዝብ ያሾፈበት የግንቦቱ የወያኔ የቀልድ ምርጫ ከተጠናቀቀ ጥቂት ሳምንታት አለፉ ። በምርጫው እንዲሳተፉለት ወያኔ ፈቅዶላቸው የነበሩ ድርጅቶችም ከሁለት ያጣ ጎመን ሆነው አረፉት። ከታሪክ ወቀሳና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ነቀፋ ነፃ ሳይሆኑ ቀሩ ። የፀፀት ሳይሆን ፥ የቁጭት እንፋሎት እየገረፋቸው ነው ። የኢትየጵያ ሕዝብም ፡-

" ደጅ ጠኝ ሆኑ በወያኔ ሜዳ ፥
በየኤምባሲው ጓዳ፥
እጁ እንደተያዘ ከብቱ እንደተነዳ ። "

እያለ ያፌዝባቸዋል። ትዝብቱንም ይገልጻል። የወያኔ ሰለባዎች በመሆናቸው፥ ምናልባት ያዝንላቸው እንደሆን እንጅ አያዝንባቸውም። ምክንያቱም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ለዜጎቹ ሁሉ የኀሊና ፍርድ የማይነፍግ ሕዝብ ስለሆነ ነው።

" ሕዝበ ኢትዮጵያ አባ ደፋር፥
እያየህ ውኃ እያየህ ማር ። " የሚባልለትም ለዚሁ ነው እኮ !

ከአንድ ብሄር የተውጣጡ ጥቂት ዘረኞች ያቋቋሙት የአፓርታይድ አምባገነን ሥርዓት፤ ኢትዮጵያ በአሃዳዊ ፓርቲ ስር እንድትሆን የግንቦቱ የወያኔ ምርጫ እንደገና አረጋግጧል። በወያኔና በደርግ መካከል ያለ ልዩነት የጌቶቻቸው መቀያየር ብቻ ነው ። ደርግ ሀገራችንን የቀድሞዋ ሶቬየት ኅብረት የጅ አዙር ቅኝ ግዛት አድርጎ አስራ ሰባት ዓመታት በአንድ ያምባገነን ፓርቲ ስር አስገብቶ ተዘርዝሮ የማያልቅ ብሄራዊ ወንጀል ከፈፀመ በኋላ ሀገር

አጥፍቶ ጠፋ ። አለቆቹም እንኳን ደርግን እራሳቸንም ሳያድኑ ቀሩ። እነርሱ ከጠፉ በኋላ ቀጥቅጠው ሲገዙትና ሲያዝገዙት የነበረው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠረው ሕዝብ ቢያንስ በአንዳንድ ቦታዎች የይስሙላ ነፃነቱን አግኝቶ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር በቅቷል ። አንፃራዊ በሆነ መልኩም ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እያካሄደ የራሱን ብሄራዊ መንግሥት ለመመስረት ችሏል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ለዚህም አልታደለም ። የመከራ ገመዱ ገና አልተቆረጠም ። መታደልን ከመታገል ጋር ካላዋኻደ በስተቀር መከራው ይቀጥልበታል እንጅ እንደማይቀነስለት የግንቦቱ የወያኔ ምርጫ አረጋግጦለታል ። ደርግ ለሶቪየቶች እሽክርና ተቀጥሮ የሀገሩን ሉዓላዊነት እንደ ሸጠ ሁሉ ፥ ወያኔም በተመሳሳይ መልኩ ሀገራችንን የምዕራባውያን የእጅ አዙር ቅኝ ተገዥ አድርጓታል ። ታማኝ አገልጋይነቱን በግንቦቱ ምርጫ ስለአረጋገጠላቸው ፥ ምርጫው በተፈፀመ ማግስት የአንድ ቢሊዮን ዶላር ዕርዳታ መዕውተውታል ። አበጅህ ልጃችን ለማለት ነው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ የግንቦቱ ምርጫ ባኋላ በድጋሚ ያረጋገጠው አንድ ሀቅ ቢኖር፥ የራሱን ዕድል የሚወስነው እርሱ ራሱ ባለቤቱ እንጅ፥ባዕዳንም ሆኑ የባዕዳኑ ጋሻ ጃግሪዎች አለመሆናቸውን ነው። በመሆኑም ይህ ክስተት እንደገና የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል እንዴት መመራት እንዳለበት የሚያሳይ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የመጀመሪያውን ገፅ ሊይዝ የሚገባው፥ እስካሁን ትግሉ የተጓዘባቸውን ሂደት ፥ ስልቶችና ስትራተጂዎች ወይም ዓላማዎችን በሚገባ ያጤነና የመረመረ እንደሚሆን ሁሉም ይስማማበታል ። ያ ሁሉ የሰው ህይወት ጠፍቶ ፥ ብሄራዊ ሀብት-ንብረት ወድሞ፥ ሀገርና ሕዝብ በታሪካቸው ያላጋጠማቸውን ውርደትና ጥቃት ደርሶባቸው፥ ትግሉ ለምን ግቡን ሊመታ አልቻለም ? ብሎ መጠየቅ፥ ወቅታዊና አንገብጋቢ የሕዝብ ትኩረት ሆኗል ። ይህ ወቅታዊ- ሀገራዊ ጭንቀት ደግሞ ለሀቀኛ ትግል የሚሰውት ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን የማነኛው ዜጋ ጥያቄ ሁኗል ። ከድሕረ ግንቦት ምርጫ በኋላ የኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከዐ-ምድር የተለየ መልክ እየያዘ መጥቷል። የዴሞክራሲ ተስፋ ጭላንጭል ቀርቶ፥ ከድቅድቁ የጭለማ ዋሻ መጨረሻ ሊታይ የሚችል የሰላማዊ ትግል የብርሃን ወጋገን እንኳ ድርግም ብሎ ጠፍቷል ።በሁለት ባላዎች ተመርኩዘው አንዱ ሲሰበር በሌላው ተንጠልጠል እያሉ ሲወገረገሩ የነበሩት የወያኔ አጃቢዎች በሙሉ ፋይዳ-ቢስ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡ ፡ታማኝ ተቃዋሚነታቸው ወደ ደጀ-ጠኝነት ደረጃ ወርዷል ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ራሱን ከባርነት ቀንበር ሊያወጣ የሚችለው እራሱ ብቻ እንደሆነ በማያሻማ መንገድ አረጋግጧል ። የሰብዓዊ መብቶች ተከራካሪ ተቋማት ጩኸትና አቤቱታ ፤ ዘገባና ተማፅኖ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዳረደው ታውቋል ። ወያኔን በምርጫ እናሸንፈዋለን ሲባል የነበረው ትጥቅ አስፈችና ተንበርካኪ መፈክር ሁሉ የሀፍረት ማቁን ለብሶ ቀርቷል ። የሰላማዊ

ትግል ብቻ ነው የሚያዋጣው ሲሉ የነበሩት ሁሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንጀቱን ቆርጠዉታል ::ያጎረሳቸውን እጁን ነክሰውታል:: በትግል ሂደት አስፈላጊነቱ የሚያጠያይቅ ባይሆንም÷ሰላማዊ ሰልፍ÷ በሕዝባዊ አመፅ ካልተደገፈ÷ የረሀብ አድማ÷ የሻማ ማብራት ÷ የጾም የፀሎት÷ የሀዘንና የትካዜ ተቃዉሞዎች ሁሉ ወደ አርዕድ አንቀጥቅጥ ሕዝባዊ ቁጣ እስካልተለወጡ ድረስ ÷ በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ይመጣል ተብሎ እንደማይታሰብ ይኸው እንደገና ተረጋግጧል:: በአሁን ወቅት÷ ሀገር ወዳድ ምሁራንና ሕዝባዊ ተቋማት÷ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጭምር ከእንግዲህ በኋላ የትግሉ ጥሪ ተደራጅተህ አጥቃ ሊሆን እንደሚገባው እያሳወቁ ናቸው :: እየተደራጁ መታገል÷ እየተሰዉ መምታት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ አይደለም :: አዲሱ የትግሉ ምዕራፍ የሚያተኩረው በብሔራዊ ሀገርን የማዳን ትግል ዓላማ ላይ መሆን እንዳለበት ሁሉም አምኖበታል :: የትግሉ ጥሪ ብሔራዊ ÷ አሰላለፉ ሀገራዊ ÷ዒላማው በሀገር ጠላት ላይ ብቻ ያተኮረ እንደሚሆን ይህ የከሸፈው የወያኔ የግንቦቱ ምርጫ በማያሻማ መንገድ አረጋግጦታል :: ሁለት እግሮች አሉን ብለው ከሁለት ዛፎች ላይ ለመንጠጠል የሞከሩት ሁሉ ዛሬ ÷ እንኳንስ ለሁለት ዛፎች ይቅርና በአንድ ዛፍ የሚንጠላጠሉበት ባላ የላቸውም ::ከእንግዲህ ወዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል አቅጣጫ ÷ ይዘትና ሂደት ÷ ዓላማና ግብ አንድ ብቻ መሆኑን ሊረዱ ይገባል :: ከአሁን በኋላ÷ ወያኔን በምርጫ ሂደትና በሰላም ብቻ እየታገልን እናወርደዋለን የሚባለውን ያረጀ-ያፈጀ አመለካከት መሰረዝ አለባቸው ::ይህን ካላመኑ ግን ቢያንስ የትግሉ እንቅፋቶች እንዳይሆኑ በኢትዮጵያ ሕዝብ በኩል እየተጠየቁ ነው :: ለወያኔ ሽፋን እየሰጡ የሕዝቡን ትግል ለማኮላሸት ሲባል ጋሬጣ የሚሆኑት ክፍሎች÷ የብሔራዊ ወንጀል አባሪ- ተባባሪ እንደሆኑ ሊገነዘቡት ይገባል :: ከእንግዲህ ወዲህ ሽፋን እየሰጡ መቀጠል ጊዜው አልፎበታል :: በዚህ በአዲሱ የትግል ምዕራፍ ሊካተቱ የሚችሉት÷ ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ጠላት መሆኑን አምነው ይህን የወገን ጠላት ለማስወገድ ማንኛውንም መስዋዕት ለመክፈል ፈቅደው የተዘጋጁ ሊሆን ይገባል :: ከአሁን በኋላ ÷ ማቂን ጨርቄን የሚባል ነገር የለም ::

ሀገራችን በረዥም ጊዜ ታሪኳ፤ ወያኔን የመሰለ የወገን ጠላት አጋጥሟት እንደማያውቅ÷ ማንኛውም ዜጋ አምኖበታል:: የወገን ጠላት የሆነውን ይህን ዘረኛ ቡድን ከማስወገድ በቀር ሌላ ምርጫ እንደማይኖረው የወሰነውም÷ይህ የወገን ጠላት የሆነው ቡድን ከባዕዳን ጠላቶች ጋር አባሪ ተባባሪ በመሆን ሀገሩን እያጠፋበት በመሆኑ ነው:: ዛሬ ባዕዳን ጠላቶቹ÷ ከወያኔ ጋር ስለተባበሩ÷ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዚህ በመከራ ዘመኑ ሊረዳው የሚችል የውጭ ኃይል አልተገኘም:: ታሪክን ማስታወስ ካለብን÷ በ1928 ዓም ሀገራችን በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ጦር ስትጠቃ÷ ዓለም በሙሉ የፍርሃት ፊቱ ሲያዞርባት አራት ሀገሮች ብቻ የሞሶሊኒን

ወረራ በመቀወማቸው ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለውለታዎቹ እንደነበሩ ያምናል። በወቅቱም የአክብሮት ምስጋናውን አስተላልፎላቸዋል። እነኝህ ሀገሮች፡-

1ኛ ሩሲያ 2ኛ. ሜክሲኮ 3ኛ.ሰሜን አማሪካ 4ኛ. ኔውዚላንድ ነበሩ ።

ይህ የዛሬው ትውልድም በበኩሉ፥ ከጀግኖቹ አባቶቹና እናቶቹ የወረሰውን ታሪክ ማስታወስ እንዳለበት ቢገነዘብም፥ በፖለቲካ ሂደት ፥ ቋሚ ወዳጅም ሆነ ቋሚ ጠላት እንደማይኖር ደግሞ አበክሮ ይረዳል። ባሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ የቅርብ ጎረቤትም ይሁን የሩቅ ዘመድ ወዳጅ እንደሌላት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቸውም ሁኔታና ዘመን በበለጠ አውቋል።በአንፃሩ ደግሞ <u>ቋሚ ጥቅም ብቻ</u>፥ የዓለም አቀፍን ፖለቲካና ዲፕሎማሲ እንደሚያሽከረክረው ይገነዘባል ። ዛሬ ምዕራባውያኑም ሆኑ ሌሎች ቡድኖች ለራሳቸው ዘላቂ ጥቅም ብቻ ሲሉ ወያኔን እንደመሳሪያ እየተጠቀሙ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ንጹህ ደም እጃቸውን ነክረዋል። ይህ የሕዝባችን የጓጎለ ደም ጩኸት ፥ ምድራዊ ዳኛ አጥቶ ወደ ሰማየ- ሰማየት አቤቱታውን በማሰማት ላይ ይገኛል። የኢትዮጲያ ሰማዕታት አፅምም በበኩሉ ኤሎሄ ! ኤሎሂ ! ማለቱን አላቆመም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሠላምና ፀጥታ ፥ ፍትኅ-ርትዕ እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስከሚጎናጸፍ ድርስ ጩኸተና ትግሉ ይቀጥላል። ይህን ብሔራዊ ጩኸትና ሀገራዊ እሮሮ ማቆም የሚችለው ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው። “ ቤታቸውን ከፍተው በሌባ ያምርራሉ ” ሆነና እኛው ራሳችን ሳንደራጅ፥ ሳንስማማ፥ ሳንተበባርና ተጠናክረን ሳንቆም እየቀረን ፥ ወያኔ አጠቃን፥ ባዕዳን በደሉን እያልን፥ በዋናውን ምክንያት ላይ ሳናተኩር ጊዜያችንን አሳልፈናል። አንዱ በሌላው ላይ ጣት በመቀሰር ፥ የአንድነት ትግል ቀርቶ አብሮ መኖር እንኳ የሚቻል አይሆንም ።ይህ አሁን የተከፈተው አዲስ የትግል ምዕራፍ፥ከማናኛው ጉዳይ ባላነሰ ሊያምንበት የሚገባው ነገር ቢኖር፥ወያኔ ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደ ገል ቀጥቅጦ “ ሊገዛ ” የበቃው፥ በራሱ ችሎታ ሳይሆን፥ በኛው በራሳችን ድክመትና መለያየት ምክንያት መሆኑን ነው ። ይህን እንደ እንቆቅ የሚጎመዘዝ ሀቅ ተቀብሎ ለጋራ ትግል መዘጋጀት፥ለአዲሱ የትግል ምዕራፍ የመጀመሪያውን ገፅ ከፋች ይሆናል ። ካለፈው የትግል ሂደት መማር ካለብንና ብሎም፥ ኢትዮጵያ ከወያኔ ጭቆና ነፃ መውጣት አለባት ከተባለ፥ መተኮር ያለበት በአለፈው ስህተትና ድክመት ላይ ብቻ ሳይሆን ፥ በወደፊት ጥንካሪያችንና ኃይላችንም ላይ ነው ። ኃይላችንን በማይጠቅም መድበል አስቀምጠን ፥ አንደኛው ከሳሽ ፥ ሁለተኛው ተከሳሽ፥ ሦስተኛው ዳኛ አራተኛው ጠበቃ እየሆንን ሀገራችንን የምናድንበትን ኃይል፥ ጊዜ፥ ሀብትና ጉልበት አባክነናል ። ይህ በዚህ አሁን በተከፈተው የትግል ምዕራፍ ቦታ አይኖረውም ። ይህ አዲሱ የትግል ምዕራፍ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ዐብይ ትኩረትና ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይጠበቅበታል።

- የኃይሎች አሰላለፍ ማካተት የሚገባው የኢትዮጵያን አንድነት ያነገቡ ሀገር ወዳዶችና ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች እንደሆኑ ማረጋገጥ፥

- ወያኔን ማስወገድ የቅድሚያ የትግል ግባቸው ያደረጉ ኃይሎች ጎራ መሆኑ የታመነበት፥

- በጋራ የትግል ስልትና ዕቅድ/ግብ የሚስማሙ፥ ወገኖች መሆን እንደ ሚገባቸው፥

- በብሄራዊ አርነት ትግል ብቻ ሳይሆን፥ ለሀገራዊ ነፃነት፥ ለዜጎቿ እኩልነትና አንድነት፥ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ማመናቸውን ያረጋገጡ ተጠራርተው ውይይት መጀመር እንዳለበቸው የወቅቱ አንገብጋቢና አጣዳፊ ሀገራዊ ጉዳይ ነው ብለን እናምናለን፡፡

በመሆኑም፥ ለዚህ አዲስ የትግል ምዕራፍ መነሻ የሚሆን ውይይት እንዲጀመር በዓላማ ለሚያምኑ ኃይሎች ሁሉ ጥሪው ይተላለፍላቸዋል፡፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነቱና በነፃነቱ ለዘለዓለም ይኖራል !!!!!!